የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

አንደኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
አዲስ አበባ - መስከረም ፪ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

First year No .11
Addis Ababa 12[th] Sep. 2009


<u>ማውጫ</u>


**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ አዋጅ**


<u>**Contents**</u>


**The Addis Ababa City Governments Technical and Vocational Education and Training Agency Proclamation**


***አዋጅ ቁጥር ፲፩/፪ሺ፪ ዓ.ም***

***የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ***

በሀገሪቱ ብቁ ተነሳሽነትና የፈጠራ ችሎታው የዳበረ በክህሎት የተካነ የሰው ኃይል በመፍጠር በሀገሪቱና በከተማችን ድህነትን በማስወገድ ለኢኮኖሚያዊ እድገት አስተዋፅኦ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና በባህሪው የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ስፊ ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ ለዚህ ሥልጠና ቴክኒክና ሙያን በብቃት የሚመራ መንግስታዊ አካል በከተማ አስተዳደር ደረጃ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ፲፬ (፩) (ሀ) እና በፌደራል መንግሥት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አዋጅ ቁጥር ፫፻፺፩/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ፳፮(፪) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

***Proclamation No. 11/2009***

***The Addis Ababa City Government Technical and Vocational Education and Training Agency Establishment Proclamation***

**WHEREAS,** it is found necessary to alleviate poverty in the City and the country and contribute to the economic growth through creating inspired, creative, and skillful manpower;

**WHEREAS,** it is found necessary to establish a governmental entity at the level of City Government that would oversee the technical and vocational capacity of the trainings as the technical and vocational education and training by its nature requires the active participation of governmental and non governmental organizations;

**NOW, THEREFORE,** the Addis Ababa City council in accordance with Article 14(1) (a) of the Addis Ababa City Charter Proclamation No 361/2003 and Article 26(2) of the Federal Government Technical and Vocational Education Training Proclamation No 391/2004 has issued this proclamation as follows;


ያንዱ ዋጋ..
Unit Price 21.83

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፳፬፵፭
Addis Negari Gazeta 2445

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ «የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፩/፪ሺ፩»ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አግባብ ሌላ ካልሆነ በስተቀር፣

፩. "አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፣

፪. "ካቢኔ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ነው፣

፫."ኤጀንሲ" ማለት በዚህ አዋጅ የተቋቋመ የአስተዳደሩ፣የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ነው፣

፬. "ተቋም" ማለት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በደረጃ ፩ በደረጃ ፪ በደረጃ ፫ እና ሌሎች ገበያ ተኮር የሆኑ አጫጭር ሥልጠናዎችን የሚሰጥ መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ሕጋዊ ተቋም ነው፣

፭. "ኮሌጅ" ማለት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና

ሀ.በደረጃ ፩

ለ.በደረጃ ፪

ሐ.በደረጃ ፫

መ.በደረጃ ፬

ሠ.በደረጃ ፭ እና ሌሎች የገበያ ፍላጎት መሠረት ያደረጉ አጫጭር ሥልጠናዎችን የሚሰጥ መንግሥዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ሕጋዊ የሥልጠና ኮሌጅ ነው፣

፮. "ዕውቅና" ማለት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጣን ብመስጠት ተግባር ላይ የተሰማራ ማስልጠኛ ተቋም ወይም ኮሌጅ ሥልጠና ለማካሄድ የሚሰጠው የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ መረጃ ነው፣

## Part one
## General

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as «The Addis Ababa City Governments Technical and Vocational Education and Training Agency Establishment Proclamation No. 11/2009»

**2. Definitions**

In this proclamation unless the context requires otherwise:

1. **"Government"** means the Addis Ababa City Government;
2. **"Cabinet"** means the Addis Ababa City Government cabinet;
3. **"Agency"** means the Addis Ababa City Government Technical and Vocational Education and Training Agency established in accordance with this proclamation;
4. **"Institution"** means governmental or non governmental legal entity that provides level 1, 2, 3, and other market oriented short term trainings;
5. **"College"** means legal governmental or non governmental training college that provides trainings at the following levels
   a. level 1
   b. level 2
   c. level 3
   d. level 4
   e. Level 5 and other market oriented short term trainings.
6. **"Recognition"** means document approving the capacity of a training institution or college engaged in providing technical and vocational education and training to conduct training;

**፯. የካውንስል መቋቋም**

ኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባሩን በብቃት መወጣት ይችል ዘንድ ምክርና እገዛ የሚሰጥ የአስተዳደሩ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ካውንስል በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

## ክፍል ሶስት
## አላማ፣ ስልጣንና ተግባር

**፰. ዓላማ**

ኤጀንሲው የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል:-

፩. የከተማውን ማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ እድገት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በአግባቡ ተደራጅተውና ጥራታቸው ተጠብቆ በዘላቂነት እንዲካሄዱ ማድረግ፣

፪. የከተማው ነዋሪዎች ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ስልጠና ማግኘታቸውን የሚሰጡትም ስልጠናዎች የሀገሪቱንና የከተማውን አስተዳደር የልማት ትልምና የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎትን መሠረት ያደረጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

፫. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ምርምርና ሥልጠና የሚያጎለብት ከተማ አቀፍ አቅም መገንባት፣

፬. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የቴክኖሎጂ ሽግግርና የፈጠራ ማዕከላት እንዲሆኑ ማስቻል።

**፱. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩. የሀገሪቱን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስትራቴጂና መርሃግብር በከተማው ደረጃ ለማስፈጸም የሚያስችሉ ወቅታዊ እቅዶችን ያዘጋጃል፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሚያጎለብቱ ፕሮጀክቶችን ያዘጋጃል፣ ሲጸድቁም ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

፪. በአገር አቀፍ ደረጃ የወጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሙያ ደረጃዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

፫. በሚወጣው አገር አቀፍ መመሪያ መሠረት የመካከለኛ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች በከተማ ውስጥ መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፣

፬. በኤጀንሲው የሚዘጋጁ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ሥርዓተ-ትምህርቶች በከተማው ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣



**7. Establishment of the Council**

The Technical and Vocational Education and Training Council that would provide counseling and assistance with the view to ensure the effectiveness of the Agency is hereby established.

## Part Three
## Objective, Power and Function

**8. Objectives**

The Agency shall have the following objectives:-

1. Ensuring the quality and sustainability of technical and vocational training that would contribute to the implementation of the social and economic development objectives of the City;
2. Ensuring that dwellers of the City get proper training and that the trainings are offered on the basis of the development objectives and skilled man power needs of the City and the country;
3. Building city-wide capacity that would develop research and training in the area of technical and vocational education and training;
4. Enabling technical and vocational education and training institutions to be centers of creativity and technological transfer.

**9. Powers and Functions of the Agency**

The Agency shall have the following powers and functions:-

1. Prepare timely plans for the implementation, at the City level, of the country's technical and vocational education and training strategy and action plan; prepare projects that would improve technical and vocational education and training, and upon approval ensure their implementation;
2. Ensure that national technical and vocational education and training professional standards are properly implemented;
3. Ensure that medium term technical and vocational education and training programs implemented nationwide are organized in the City;
4. Cause the implementation, in the City, of the technical and vocational education and training curriculum prepared by the Agency;

ሀ. መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ /አጫጭር/ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠናዎችን በሚመለከት ሥርዓተ-ትምህርት እንዲዘጋጅና እንዲተገበር ያደርጋል፤ ይቆጣጠራል፤

ለ. በከተማው የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች አጥንተው በሚያቀርቡት የውሣኔ ሃሳብ መሠረት አዳዲስ የሥልጠና መስኮች ለመክፈት ሲፈልጉ ኤጀንሲው እንዲከፈቱ ፈቃድ ይሰጣል፣

፭. የማሰልጠኛ ተቋማት እንዲመሩባቸው የወጡና/ ወይም የሚወጡ መመሪያዎች በከተማው ውስጥ በሚገኙና የሚቋቋሙ የማሰልጠኛ ተቋማት ተግባራዊ መደረጋቸውን ይቆጣጠራል፣ እንዲሁም የማሰልጠኛ ተቋማትን እውቅና አሰጣጥ በሚመለከት የሚወጡ አገር አቀፍና የአስተዳደሩ መመሪያዎችን በከተማው ውስጥ ተግባራዊ ያደርጋል፣

፮. በከተማው ውስጥ የሚካሄዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናዎች የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ማዕከልን ያደራጃል፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ክህሎት ምዘና አፈጻፀም መቆጣጠርን ጨምሮ በከተማው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥራት መኖሩን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፯. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የቴክኖሎጂ ሽግግርና የፈጠራ ማዕከላት እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፣

፰. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ማጠናቀቂያ ማስረጃ አሰጣጥን በሚመለከት የሚወጣው አገርአቀፍ መመሪያ በከተማው ውስጥ በሚካሄዱ የቴክኒክና ሙያ ስልጠናዎች ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤

፱. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ከማምረቻና ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር ተቀናጅተው የሥራ ላይ ልምምድ በተገቢው መንገድ እንዲተገበር አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፣ ያስተባብራል፣

a. Cause the preparation of curriculum and control implementation of regular and non regular (short term) technical and vocational trainings;

b. Authorize technical and vocational education and training colleges in the City to offer new training areas based on the study and recommendations of the colleges.

5. Supervise the implementation of guidelines issued and to be issued to training institutions in the City; implement, in the City, directives of the City Government and of the country concerning recognition of training institutes;

6. organize center of competency for the technical and vocational education and trainings undertaken in the City; supervise and monitor implementation of technical and vocational education and training skill evaluation and quality of technical education and vocational training in the City;

7. Provide, in collaboration with relevant stakeholders, the proper support for technical and vocational education and training institutions to make them centers of creativity and technological transfer;

8. Ensure the implementation, in technical and vocational trainings being undertaken in the City, of national directives concerning technical and vocational education, and provision of training completion documents;

9. Coordinate and give the necessary support so that practical on-job trainings would be prepared for technical and vocational education and trainings in collaboration with manufacturing and service rendering institutions;

፲. በከተማው ውስጥ የሚካሄዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች ከከተማው አስተዳደር የልማት ትልምና የሰው ኃይል ፍላጎት ጋር በተጣጣመ መልኩ መካሄዳቸውን ይከታተላል፤ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ከከተማው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የሰው ኃይል ፍላጎት ጋር እንዲጣጣም ለማድረግ የሚያስችሉ የሙያ ገበያ ፍላጎትና ሌሎችንም ጥናትና ምርምሮች ያካሂዳል፣ እንዲካሄዱ ያደርጋል፤ ያስተዋውቃል፤ የጥናትና ምርምር ውጤቶች ቤተመረጃ ያደራጃል፤ለተጠቃሚዎች ክፍት ያደርጋል፤

፲፩. በከተማው ውስጥ የሚካሄዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ እንዲቻል የድህረ ስልጠና ክትትል ያደርጋል የድህረ ሥልጠና ጥናቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል፣

፲፪. በከተማው ውስጥ በሚካሄዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ሴቶችና አካል ጉዳተኞች ልዩ ትኩረት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ በዚህ ረገድ የሚቀየሱ አገርአቀፍ ስርአቶች በከተማው ውስጥ ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

፲፫. በከተማው ውስጥ ለሚካሄዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትና ኮሌጆች የደረጃ ብቃት ማረጋገጫና የእውቅና ፈቃድ ይሰጣል፤ በሚወጣው ደንብ መሠረት ከደረጃ በታች የሆኑትንና የሥልጠና ጥራት ላይ ችግር ያለባቸውን ተቋማት የዕውቅና ፈቃድ ይሰርዛል፤

፲፬. የአስተዳደሩን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች በበላይነት ይመራል ያስተባብራል፤ እንዲሁም ቦርዶች በአስተዳደሩ ኮሌጆችና በተቋማት ደረጃ በህግ መሠረት መቋቋማቸውን ይከታተላል አደረጃጀትንና አስተዳደራቸውን እያጠና እንዲሻሻል ለሚመለከተው ያቀርባል፣ የሥልጠና አካሄዳቸውንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፲፭. የአስተዳደሩ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች ዲኖችንና ምክትል ዲኖችን የትምህርት ዝግጅት የሥራ ልምድና ብቃትን በመገምገም የየኮሌጁ ቦርድ አስተያየት እንዲሰጥበት በማድረግ ለከተማው ከንቲባ አቅርቦ እንዲሾሙ ያደርጋል፤ በሥራ አፈፃፀም ብቃት ማነስ፣ ወይም በሙያ ሥነ-ምግባር ጉድለት ምክንያት ዲኑን ወይም ምክትል ዲኖቹን ከኃላፊነት ማሰናበት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኤጀንሲው ከሥራ እግዶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለከተማው ከንቲባ ከአስተያየት ጋር ያስተላልፋል፤

10. Follow up that technical and vocational education and training programs in the City are undertaken in conformity with the development objectives and man power demands of the Government; conduct, make conduct and promote market demand and other studies and researches that would ensure the conformity of technical and vocational education and training programs with the City's social and economic man power demands; organize data base of findings of studies and researches; make the same accessible for users;

11. With the view to ensure the efficiency of technical and vocational education and training programs in the City execute post-training follow up; enable the conduct of post-training studies;

12. Ensure that special attention is given for women and handicapped in technical and vocational education and trainings given in the City; ensure the implementation of relevant national procedures;

13. Provide capacity approval and recognition documents for technical and vocational education and training institutions in the City; based on the qualification standard regulation, nullify recognition documents of those institutions that are below standard and that have problems on training quality;

14. Superiorly direct and coordinate technical and vocational education and training colleges of the Government; fallow up that boards are legally established in the colleges and institutions of the Government submit to the relevant body recommendations on the improvement of their structure and management, follow up and control their training mechanisms;

15. Upon evaluating the educational and professional experience and capacity of the deans and deputy deans of technical and vocational education and training colleges and including the comments of the boards of the colleges, submit the same to the Mayor for appointment; In situations where, due to lack of efficiency or lack of professional ethics, the dean or the deputy deans should be removed from their position, the Agency shall submit the same with recommendations to the Mayor.

፲፮. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና ኮሌጆች የምርት ማዕከላትን በማቋቋምና የገቢ ማዳበሪያ ሥርዓት በመዘርጋት የውስጥ ገቢያቸውን የሚያዳብሩባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣

፲፯. የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን በሙያቸው ተደራጅተው ወደ ሥራ በሚገቡበት ጊዜ ያላቸውን የሙያ ክፍተት በመለየት ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት በየደረጃው ሙያዊ እገዛ እንዲደረግላቸው አስፈላጊውን የሥራ ትብብር ያደርጋል እገዛ መደረጉን ይከታተላል፣

፲፰. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን አስመልክቶ ለሕብረተሰቡ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣ ያስተባብራል፣

፲፱. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የለውጥ ሥራዎች ላይ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የሚሰለጥኑ ባለሙያዎች የጨበጡትን ዕውቀት ለሚመለከታቸው ፈፃሚ ባለድርሻዎች ማስተላለፋቸውን ይከታተላል፣

፳. በከተማው ውስጥ የሚገኙ የግል ባለሀብቶች በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የሚሳተፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡ መንግሥታዊ ከሆኑና ካልሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና ኮሌጆች ጋር የጠነከረ ግንኙነት ይዘረጋል፣ያበረታታል፣ ሁለንተናዊ ድጋፍ ይሰጣል፣

፳፩. በከተማው ውስጥ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና ኮሌጆች ስርጭት የተመጣጠነ መሆኑን ይከታተላል፣ ከሚመለከታቸው ጋር በመመካከር ተጨማሪ ተቋማት የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል የሥልጠናዎችን ጥራትና ብቃት ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፣

፳፪. በከተማው ከሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና ኮሌጆች እንዲሁም ከሀገር ውስጥና በውጭ ከሚገኙ መሰል ተቋማት ጋር ግንኙነትን በመፍጠር የልምድ ልውውጥ ያደርጋል፣ የጋራ ጥቅምን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይፈራረማል፣

፳፫. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆችና ተቋማት ከተለያዩ መንግስታዊ ከሆኑና ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የትብብር ሥልጠና እንዲፈራረሙ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ይከታተላል፣

16. Facilitate conditions for technical and vocational education and training institutions and colleges to establish product centers and set up income upgrading mechanism so as to improve their internal income;

17. Provide the necessary work cooperation upon indentifying their gap and in collaboration with the concerned bodies, to the graduates of technical and vocation at the time when they involve in to job upon organization in their respective field; follow up that such support is provided;

18. prepare and coordinate awareness creation forums for the public concerning technical and vocational education and training in collaborate ion with relevant bodies;

19. Follow up that professionals trained on improvement of technical and vocational education and training locally or outside the country share their knowledge with relevant stakeholders;

20. Facilitate condition for the participation of private investors of the City in the sector of technical and vocational education and training; establish, and encourage strong relations with governmental and non-governmental technical and vocational education and training institutions and colleges and give them all-round support;

21. Ensure that the distribution of technical and vocational education and training institutions and colleges in the city are balanced; shall, in consultation with relevant bodies, facilitate the establishment of more institutions; shall confirm and control the quality and of trainings.

22. Share experiences, sign agreements of mutual benefit by establishing contact with technical and vocational education and training institutions and colleges in the City and other similar institutions in and outside the country.

23. Give the necessary support for technical and vocational education and training institutions and colleges to sign training cooperation agreements with governmental and non-governmental organizations; follow up the same;

፳፬. ከትምህርት ስርአቱ ጋር የተጣጣመ አፈጻጸም እንዲኖር ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ከአስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል፣ እንዲሁም በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ለሀገር አቀፍ ደረጃዎች፣መመሪያዎች፣ ስትራቴጂዎችና መርሃ ግብሮች የተቀናጀ አፈጻጸም የአስተዳደሩን ድርሻ በሚመለከት ከአገርአቀፉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ጽህፈት ቤት ጋር እንደየአግባቡ ተቀናጅቶ ይሰራል፣

፳፭. የካውንስሉ ሴክረታሪያት በመሆን ያገለግላል፤

፳፮.የሥራ እቅዱንና በጀቱን ያዘጋጃል፤ ሲጸድቁም ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ ወቅታዊ የተግባርና የበጀት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶችን ለከተማው ከንቲባ ያቀርባል፣

፳፯.ከካውንስሉ ሰብሳቢ ጋር በመመካከር የካውንስሉን የሥራ እቅድና በጀት ያዘጋጃል የተፈቀደለትን በጀት ያስተዳድራል፤

፳፰.የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፤ መክሰስ ወይም መከሰስ ይችላል።

## ፲. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ የተገለፀውን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል ፤

፪.ኤጀንሲውን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤

፫.የኤጀንሲውን ስትራቴጂክ የፖሊሲ ሀሳቦች ይቀርጻል፣ያዘጋጃል፣ እንዲፀድቅ ለከተማው ከንቲባ ያቀርባል፤

፬. በአስተዳደሩ የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ሕግ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

፭.የኤጀንሲውን የሥራ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል በጊዜው ያቀርባል!

፮. የኤጀንሲውን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል ሲፈቀድ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፯.ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍናና በተፈለገው መጠን የሥራ ፍጥነትን ለመጨመር ከተግባሩ በከፊል ለበታቹ ላሉ ኃላፊዎችና ለሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤

፰. በአስተዳደሩ የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሠረት ለኤጀንሲው በተፈቀደ በጀትና ዕቅድ መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል!

24. Work in coordination with the Education Bureau of the City Government to assure conformity of implementation with the educational system; work in coordination with the national technical and vocational education and training office concerning the role of the administration on integrated implementation of national standards, directives, strategies and action plans in the area of technical and vocational education and training institutions;
25. Serve as a secretariat of the council;
26. Prepare its activity plan and budget; execute the same upon approval; shall submit timely budgetary and activity implementation reports to the Mayor;
27. In consultation with the Council prepare the Council's activity plan and budget; administer the authorized budget;
28. Own property, enter into contract, sue or be sued in its own name.

## 10. Powers and Function of the Director

The Director of the Agency shall have the following powers and Functions:-

1. Implement the power and responsibilities of the Agency listed in Article 9 of this Proclamation;
2. Superiorly direct, coordinate, and control the Agency;
3. Formulate and prepare the Agency's strategic policy; present the same to the Mayor for approval;
4. In conformity with the civil servants law of the City, employ, administer and fire employees;
5. Submit the reports of the Agency to the relevant body on time;
6. prepare the annual plan and budget of the Agency and executes the same upon approval;
7. Designate some of his activities to his subordinates, with the view to bring about enhanced efficiency of the Agency;
8. withdraw money based on authorized budget and plan, in accordance with the financial administration law of the City Government;

፱.ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚደረግ ግንኙነት ኤጀንሲውን ይወክላል ፤

፲. ከከተማው ከንቲባ የሚሰጡ ተጨማሪና ተዛማጅ ሥራዎችን ይፈፅማል፡፡

**፲፩. የምክትል ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

1. በኤጀንሲው መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት ተለይተው የሚሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል፤
2. ዋና ዳይሬክተሩ በሌለበት ተክቶት ይሠራል፤
3. በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡትን የኤጀንሲውን ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል፤

## ክፍል አራት

## የካውንስሉ አደረጃጀት፤ አላማ፤ ስልጣን ተግባርና አሰራር

**፲፪. የካውንስሉ አደረጃጀት**

ካውንስሉ የሚከተለው አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

1. በከተማው ከንቲባ የሚሰየሙ የተለያዩ አካላት ተወካዮች በአባልነት የሚገኙበት የካውንስል ጉባኤ፣
2. ሰብሳቢ እና
3. የካውንስል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይኖሩታል፡፡

**፲፫. ዓላማ**

ካውንስሉ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል!

፩. በከተማው ያሉት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች የሥልጠና ዓይነቶችና ደረጃዎች አመራርና አደረጃጀት ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አኳያ መጣጣሙን በመገምገም አስፈላጊ ማሻሻያዎች ማድረግ እና ሌሎች ተጨማሪ የሥልጠና ተቋማት እንዲቋቋሙ አቅጣጫ ማስቀመጥና ማመቻቸት፤

፪. የሥልጠና ፕሮግራሞችን ውጤታማና የተሳካ እንዲሆኑ ሁሉም የባለድርሻ አካላት በፖሊሲና ዕቅድ ነክ በሆኑ ጉዳዮች የሚሳተፉበት የምክክር መድረክ እንዲኖር በማድረግ በቅንጅትና በመደጋገፍ የሚሠሩበት ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

፫. የተለያዩ የቢዝነስ ፕላኖችን በመንደፍ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት እንዲስፋፉ ዕገዛ በማድረግ ለቴክኖሎጂ ሽግግር አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር፡፡



9. Represents the Agency in relations with third parties,
10. Perform additional and related activities given by the Mayor.

**11. Powers and Functions of the Deputy Director**

1. Perform activities as identified by the structural organization of the Agency;
2. Act as the Director in his absence;
3. Perform additional activities of the Agency given by the Director.

## Part Four

## Organization, Objectives, Powers, functions and Procedures of the Council

**12. Organization of the Council**

**The council shall have the following organization:-**

1. Council forum comprised of representatives of different bodies nominated by the Mayor;
2. Chairperson;
3. Executive committee of the Council.

**13. Objectives**

The Council shall have the following objectives:-

1. Evaluating the conformity of the types, levels, management and organization of trainings of technical and vocational education and training programs in the City with the social and economic development and making appropriate amendments; and recommending and facilitating the establishment of additional training institutions;
2. Create consultation forums where all stakeholders deliberate on policy and plan related issues; with the view to make training programs efficient an fruitful, facilitating the coordination and cooperation among stakeholders;
3. Facilitating conducive conditions for technological transfer through preparing different business plans and supporting the growth of micro and small enterprises.

**፲፬. የካውንስሉ፣ ሥልጣንና ተግባር**

፩. ኤጀንሲው በዓላማው መሠረት ለሚያደርገው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ምክር ድጋፍና አመራር ይሰጣል፣

፪. ለኤጀንሲው ከፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የሚወጡትን አጠቃላይ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ አዋጆች ፣ደንቦችና መመሪያዎች በአዲስ አበባ ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዕድገት ለማፋጠን የሚያስችል ዝርዝር የአፈፃፀም ስልቶች ላይ ምክር ይሰጣል፣ ለአፈፃፀማቸው ድጋፍ ይሰጣል፣

፫. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ ዕቅድና ሪፖርት በመመርመር ምክር ይሰጣል፤

፬. የሥልጠና መስኮች በሀገር አቀፍ የልማት ትልም በአጠቃላይ እና በከተማዋ የሰው ኃይል ሥልጠና ፍላጐት ወይም ገበያ ፍላጐት መሠረት በማድረግ እንዲካሄድ ስልት ይቀይሳል፤ ምክርና ድጋፍም ይሰጣል፤

፭. በመደበኛውም ሆነ መደበኛ ባልሆነ፣ በየደረጃው ያሉ ሥልጠናዎችን በማጠናቀቅ የሚወጡትን ሠልጣኞች ከሥራ ሥምሪት አኳያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎች ልማት የማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ፣ አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም፣ የቤቶች ልማት፣ ፕሮጀክት እና ሌሎችም የሚመለከታቸው አካላት ተቀናጅተው ለሚያከናውኑት ተግባር እገዛ ይሰጣል፤

፮. ከኤጀንሲውና ከሚመለከታቸው የተወጣጡ ንዑሣን ኮሚቴዎችን እንደአስፈላጊነቱ ይሰይማል፤ በክፍለ ከተማ ደረጃም ለሥልጠናው ድጋፍ የሚሰጥ የቴክኒክና ሙያ ካውንስል እንደሁኔታው እንዲቋቋም ያደርጋል፤

፯. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በመምከር ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፣

፰. የኤጀንሲውን ዓላማ ስኬት የሚያጎለብቱ ምክርና ድጋፎችን ይሰጣል፡፡

**14. Powers and Functions of the Council**

1. Provide counseling, assistance and guidance to the Agency towards practical implementation of the objective;
2. Based on policies, strategies, proclamations, regulations and directives of the Federal Government on technical and vocational education and training and in accordance with the actual reality of Addis Ababa, provide counseling concerning detailed implementation mechanisms aimed at accelerating the development of technical and vocational education and training; and upon approval assist in the implementation of the same;
3. Examine the plans and reports in the area of technical and vocational education and training and give counseling concerning the same;
4. Design mechanism, offer counseling and assistance on the means to make trainings be conducted in conformity with the national development objectives and the man power training needs of the City or based on the market demand;
5. Assist the coordination, formation and expansion of micro and small scale enterprises development associations, Addis Loan and Saving Enterprise, house development project and other relevant bodies in the area of technical and vocational education and training with the view to ensure the employment of regular or non regular fresh graduates;
6. Assign sub committees or task forces comprised of the Agency and relevant bodies; enable, at the sub-city level, the formation of technical and vocational council, as would deem necessary that will provide assistance to the training;
7. Create conducive atmosphere by providing counseling on technical and vocational education and training issues; follow up their implementation;
8. Provide counseling and assistance with the view to enhance success of objectives of the Agency.

**፲፭. የካውንስሉ አመሰራረት**

የካውንስሉ ጉባኤ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል:-

፩. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ የሚሰየም ----------------------------------------------------ሰብሳቢ

፪. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ --- -----------------------------------ምክትል ሰብሳቢ

፫. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ------------------------------ -----------------------------------አባልና ጸሐፊ

፬. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ ----------------------------አባል

፭. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ -----------------------------------አባል

፮. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ኃላፊ ----- ---------------------------------------------አባል

፯. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ---------------------------------------------አባል

፰.አቅም ግንባታ ቢሮ ሀላፊ -----------------------------አባል

፱.ፍትህና ሕግ ጉዳዩች ቢሮ ኃላፊ ------------------አባል

፲.የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ ---------አባል

፲፩.ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ------------------------አባል

፲፪.ሴቶች ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ--------------------------አባል

፲፫.የማስታወቂያ ቢሮ ኃላፊ--------------------------አባል

፲፬.ጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎች ኤጀንሲ ኃላፊ-------- ----------------------------------------------አባል

፲፭. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሠርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር--------------------------------አባል

፲፮. የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር ፕሬዝዳንት ----አባል

፲፯. የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት----አባል

፲፰. የአዲስ አበባ ኢንዱስትሪዎች ማህበር ሰብሳቢ -----አባል

፲፱. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ----------------------አባል

፳.የኢትዮጵያ መድህን ድርጅት --------------------አባል

፳፩.የመብራት ኃይል ኮርፖሬሽን የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ - ------------------------------------አባል

፳፪፡ የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ኃላፊ ---------- ----------------------------------------------አባል

፳፫. የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊ--- ---------------------------------------------አባል

**15. Organization of the Council**

The forum of the Council shall have the following members:-

1. Nominated by the Mayor of the City Government…… …………………chairperson
2. Head of Education Bureau of the Addis Ababa City Government ……………deputy chairperson
3. Director of the Agency … Member and secretary
4. Head of the Finance and Economic Development Bureau of the Addis Ababa City Government ……………………………………...member
5. Head of the Youth and Sport Bureau of the Addis Ababa City Government ………………...member
6. Head of Health Bureau of the Addis Ababa City Government ……………………………..member
7. Construction and Urban Development Bureau of the Addis Ababa City Government …….. member
8. Head of Capacity Building Bureau of the Addis Ababa City Government ………………… member
9. Head of Justice and Legal Affairs Bureau of the Addis Ababa City Government …… ……member
10. Head of Trade and Industry Development Bureau of the Addis Ababa City Government …… ………………………………………………member
11. Head of Culture and Tourism Bureau of the Addis Ababa City Government ………………. member
12. Head of Women Affairs Bureau of the Addis Ababa City Government ……………….. member
13. Head of Information Bureau of the Addis Ababa City Government ……………………... member
14. Head of the Agency for Micro and Small Enterprises of the Addis Ababa City Government………………………….. member
15. Commissioner of the Addis Ababa City Government Civil Service Commission…… ………………………………………….member
16. President of the Youth Association of the Addis Ababa City Government ……………….. member
17. President of the Addis Ababa Chamber of Commerce…… …………………………...member
18. Chairperson of Addis Ababa Industries Association…… member
19. Commercial Bank of Ethiopia………….. member
20. Ethiopian Insurance Company………… member
21. Electric Power Corporation, Addis Ababa Branch ………………………………………… member
22. Head of Addis Ababa Water and Sewerage Authority………………………………. member
23. Head of Addis Ababa Housing Agency Project office…………………………………….member

፳፬.የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማህበር ፕሬዝዳንት----------------------------------------አባል

፳፭. የእንጦጦ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ዲን ----------------------------------------አባል

፳፮. የጄኔራል ዊንጌት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ዲን.................................አባል

፳፯. የአዲስ አበባ ተግባረዕድ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ዲን ............. አባል

፳፰. ንፋስ ስልክ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ዲን ...........................................አባል

፳፱. ምሥራቅ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ዲን.... ......................................አባል

፴. የኢትዮ-ቻይና ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ዲን---------አባል

፴፩. አቃቂ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ዲን..........................................አባል

፴፪. የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ----አባል

፴፫. የአዲስ ብድርና ቁጠባ ሕብረት ሥራ ማህበር----------------------------------------------------አባል

፴፬. ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ አባል እንዲሆኑ በካቢኔው የሚሰየሙ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

## ፲፮. የካውንስሉ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር

ሀ) ካውንስሉን በሰብሳቢነት ይመራል፣

ለ) የካውንስሉ ውሳኔዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣

ሐ) የከተማው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን በሚመለከት በማናቸውም ስብሰባ ወይም ጉባዔ ላይ የከተማ አስተዳደሩን ይወክላል።

## ፲፯. የካውንስሉ ምክትል ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር

ሀ) የካውንስሉ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ስብሰባውን በበላይነት ይመራል፤

ለ) በካውንስሉ ሰብሳቢ በካውንስሉ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

## ፲፰. የካውንስሉ ፀሐፊ ሥልጣንና ተግባር

ሀ) የካውንስሉን ጉባኤ የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፣

ለ) የካውንስሉን የስብሰባ ቃለ-ጉባዔ ይይዛል፣ ሪፖርት ያዘጋጃል፣

24. President of Private Higher Education Institutions Associations................................... member
25. Dean of Entotic Technical and Vocational Education and Training College............ member
26. Dean of General Winged Technical and Vocational Education and Training College ............member
27. Dean of Addis Ababa Tegbareid Technical and Vocational Education and Training College ..........................................................member
28. Dean of Nefas Silk Technical and Vocational Education and Training College ............ member
29. Dean of Misrak Technical and Vocational Education and Training College ........... member
30. Dean of Ethio-China Polytechnic College...... ..................................................member
31. Dean of Akaki Technical and Vocational Education and Training College ........... member
32. Ethiopia Telecommunication Corporation ..................................................member
33. Addis Loan and Saving Cooperative ...... member
34. And if necessary other members to be nominated by the Cabinet.

## 16. Power and Function of Chairperson of the Council

a) Preside over the meetings of the Council;

b) Ensure that the decisions of the Council are implemented;

c) Represent the City Government in any meetings or forums dealing with the technical and vocational education and training of the City.

## 17.Power and Function of the Deputy Chairperson of the Council

a) Preside over the meetings of the Council in the absence of the Chairperson;
b) Perform other duties given to him by the Chairperson and the Council.

## 18. Powers and Functions of the Secretary of the Council

a) Prepare the agenda of the meetings of the Council,
b) Record the minutes of the Council, Prepare reports,

ሐ) በካውንስሉ ሰብሳቢና በካውንስሉ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

**፲፱. የካውንስሉ ሴክሬተሪያት**

የካውንስሉ ሴክሬተሪያት ኤጀንሲው ይሆናል።

**፳. የካውንስሉ የስራ ዘመንና የስብሰባ ሥነ ሥርዓት**

፩. የካውንስሉ ስብሰባ በሰብሳቢው ወይም በምክትል ሰብሳቢው ሊጠራ ይችላል፣

፪. ካውንስሉ በሦስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣

፫. አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም በማናቸውም ጊዜ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፣

፬. ሰብሳቢውን ጨምሮ ከካውንስሉ አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፣

፭. ካውንስሉ ውሣኔ የሚያስተላልፈው በድምጽ ብልጫ ነው ሆኖም ድምፁ እኩል በእኩል የተከፈለ ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሀሳብ የካውንስሉ ውሣኔ ይሆናል፣

፮. ከዚህ በላይ የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው ካውንስሉ የራሱ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት መመሪያ ማውጣት ይችላል፣

፯. የካውንስሉ የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል።

**፳፩. የካውንስሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አመሰራረትና የሥራ ዘመን**

፩. የካውንስሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ለካውንስሉ ተጠሪ ሆኖ አባላቱ ፯ ይሆናሉ፣

፪. የካውንስሉ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ፣ እና ጸሐፊ የካውንስሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ሆነው በካውንስሉ ጉባኤ ያላቸው ኃላፊነት እንደቅደም ተከተላቸው ይኖራቸዋል፣

፫. ሌሎቹ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አባላት በካውንስሉ ጉባኤ ይመረጣሉ፣

፬. የስራ አስፈጻሚው ኮሚቴ የስራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል።

**፳፪. የካውንስሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር**

ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የካውንስሉን ጉባኤ የስብሰባ አጀንዳዎች አስቀድሞ በመመርመር ያጸድቃል፣

፪. የካውንስሉ ጉባኤ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣



c) Perform such other duties given by the Chairperson of the Council and the Council,

**19. Secretariat of the Council**

The Agency shall be the Secretariat of the Council.

**20. Term of Office and Meeting Procedures of the Council**

1. The meetings of the Council can be summoned by the Chairperson or Deputy Chairperson,
2. The Council shall meeting every three Months,
3. Extraordinary meetings could be summoned for urgent Matters,
4. The presence of more than half of the members in cluding the chairperson shall constitute quorum; more than half of Council members are present.
5. The Council shall pass decisions through majority vote, however if the vote is equal the Chairperson shall have a casting vote;
6. Notwithstanding the above sub articles the Council may issue directive regarding its own meeting procedures;
7. Term of office of the Council shall be two years.

**21. Organization and Term of Office of the Executive Committee of the Council**

1. The Executive Committee of the Council shall be accountable to the Council and shall have 7 members;
2. The Chairman, Deputy Chairman, and Secretary of the Council shall be members of the Executive Committee of the Council and their responsibility in the Executive Council shall be according to their hierarchy;
3. Other members of the Executive Council shall be elected by the forum of the Council;
4. The term of office of the Executive Committee of the Council shall be two years.

**22. Powers and Functions of the Executive Committee of the Council**

The Executive Committee shall have the following powers and Functions:-

1. Priory Examine and approve meeting agendas of the forum of the Council;
2. Follow up the implementation of the decisions of the forum of the Council;

፫.የካውንስሉ ሰብሳቢ ከጸሐፊው ጋር በመመካከር የሚያቀርባቸውን አስቸኳይ ጉዳዮች ተመልከቶ የካውንስሉ ጉባኤ በማይሰበሰብበት ጊዜ ውሳኔ ይሰጣል፤ በኤጀንሲው ተፈጻሚ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፣

፬. የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን በመጠቀም የሙያ ደረጃውን ለመወሰን ምቹ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ትምህርትና ሥልጠና ነክ ጥናትና ምርምር እንዲሁም የመፍትሄ ሃሳብ ይሰጣል፤ ውጤታቸውንም በመፈተሽ ተግባራዊ እንዲሆኑ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣

፭.በከተማው አስተዳደር የሚካሄደው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሀገር አቀፍን ፕሮግራም መነሻ በማድረግ በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የተዘጋጀ የራሱ የሆነ ስትራቴጂ ኖሮት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

፮. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም የሌሎች ባለድርሻ አካላት እና የአሰልጣኝ አካላት መደጋገፍ ምቹ ሁኔታ እንዲኖር ያደርጋል፣

፯.በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንቨስትመንትን ከማስፋፋት አኳያ የሥልጠና ዕውቅና ዕድሳት ማስፋፋትና ምትክ አሰጣጥ ተግባራትን ይመረምራል፤ ኢንቨስትመንት የሚስፋፋበትን ሃሳብ ያቀርባል፣

፰.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማጠናቀቂያ እና የሙያ ብቃት ምዘና ወይም ክህሎት ምዘና በተገቢው መንገድ መተግበሩን ክትትል ያደርጋል በአጠቃላይ የሥልጠና ፕሮግራሞች ደረጃቸውን ጠብቀው መካሄዳቸውን ይከታተላል፣

፱.ለሥርዓተ ትምህርቱ ትግበራ መሻሻልና ለሥልጠና ጥራት መረጋገጥ የባለ ድርሻ አካለትን በማስተባበር ድጋፍ እንዲያገኙና ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል፣

፲.የሥልጠናው ግብዓት ማለትም የመምህራን አቅም ከፍ ማድረግን የማሰልጠኛ መሣሪያዎች መሟላትን በአጠቃላይ የማሰልጠኛ ተቋማት ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ አቅጣጫ ያስቀምጣል ለተግባራዊነቱም ድጋፍ ይሰጣል፣

፲፩.ከሥልጠና ይዘት አኳያ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ወሳኝ ድርሻ ያለው ኢንተርንሽፕ የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖረው አሳታፊ በሆነ መልኩ ደንብ እንዲወጣለት አሰሪዎችን እና በአጠቃለይ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር በተሟላ መልኩ ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍና ጥረት ያደርጋል፣

3. In consultation with the Council's Secretary, Pass decisions on urgent issues at times where there are no meetings of the Council, and ensure the implementation of the same by the Agency;
4. Facilitate the identification of level of profession by employing different evaluation techniques; conduct studies and research relating education and training; provide solutions, give direction for their implementation;
5. Enable the preparation of the strategy of the technical and vocational education and training of the City Government through the participation of stakeholders and ensures its implementation based on the national program;
6. Ensure mutual support between other stakeholders and training bodies in technical and vocational education and training programs;
7. Examine activities of training recognition renewal expansion and replacements with regard to promoting investment on technical and vocational education and training; provide suggestions on the promotion of investment in the area;
8. Monitor the proper execution of the provision of documents of completion of technical and vocational education and training, and evaluation of professional capacity or skill; shall monitor, in general, the proper implementation of training programs;
9. Coordinate stakeholders and facilitate their assistance with the view to ensuring improvement of the implementation of the educational system and quality training;
10. Give directions on the input of the training that is upgrading of capacity of teachers, fulfilling training equipments, and ensuring the standard of training institutions; and assist in the implementation thereof;
11. In collaboration with employers and other stakeholders, Make efforts and provide assistance to ensure that internship, that plays an important role in technical and vocational education and training in terms of the content of training, has legal framework and be regulated and fully implemented;

፲፪.የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት በተለይ የመንግሥት የሆኑት ገቢያቸውን እንዲያዳብሩ ወጪ ቆጣቢ ስልት እንዲከተሉ፤ የወጪ መጋራት አሰራርን በፌዴራል መንግሥት ከተዘጋጀው ስትራቴጂ በመነሳት ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ተግባራዊ እንዲሆን ምክርና ድጋፍ ይሰጣል የአፈፃፀም አቅጣጫ ያስቀምጣል፤

፲፫.ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥናት የሚዘጋጁ ፕሮጀክቶችን በመመርመር አቅጣጫ ያስቀምጣል ሲፈቀድም ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍ ይሰጣል፣

፲፬.ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በድህረ ሥልጠና የሥልጠና መስኮች በሥርዓተ ትምህርት ይዘትና ትግበራ እና በሥራ ገበያ ሁኔታ የታለመላቸውን ግብ መምታታቸውን ለማረጋገጥ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል በሚገኘውም የግምገማ ውጤት ቀጣይ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣

፲፭.የካውንስሉን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ በየሩብ ዓመቱ ለከንቲባው ጽህፈት ቤት በሰብሳቢው አማካኝነት ሪፖርት ያቀርባል፤

፲፮. ስለስራ አፈጻጸሙ ለካውንስሉ በሰብሳቢው አማካኝነት ሪፖርት ያቀርባል።

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳፫. የበጀት ምንጭ

የኤጀንሲው በጀት ከሚከተሉት ሊገኝ ይችላል፦

፩.ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚመደብ በጀትና፣

፪.ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚገኝ ድጐማ ይሆናል።

### ፳፬. የሂሣብ መዛግብት አያያዝ

፩. ኤጀንሲው ትክክለኛ የሆኑና የተሟሉ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል፣

፪.የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብት በአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር ወይም እንደአሥፈላጊነቱ እሱ በሚወክላቸው ሌሎች ኦዲተሮች በየአመቱ ይመረመራል።



12. Give counseling and assistance aimed at the implementation of cost sharing procedures based on the strategy prepared by the Federal Government and in conformity with the practical situation of the City with the view to promoting cost saving methods and improve income in technical and vocational training institutions particularly in governmental institutions, and provide direction on implementation of the same;
13. Examine projects prepared for the study of technical and vocational education and training and provide direction; assist in implementation upon approval;
14. Monitor the implementation of post-training of the training fields in technical and vocational education and training so as to ensure their success in achieving the goals in curriculum content and implementation as well as market; on the basis of the findings of the evaluation; provide direction;
15. Submit a quarterly report on the activities of the Council to office of the Mayor through the Chairperson;
16. Submit report to the Council on the activities of the Council through the Chairperson.

## Part Five
## Miscellaneous Provisions

### 23. Source of budget

The budget of the Agency could be obtained from the following sources:-

1. From Budget allocated by the Addis Ababa City Government and;
2. Subsidy from different governmental and non governmental organizations;

### 24. Keeping of books of accounts

1. The Agency shall keep authenticated and complete accounting records;
2. The accounting records of the Agency shall be audited annually by the General Auditor of the City Government or, as appropriate, by other auditors assigned by him if it's found necessary.

**፳፭. የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ**

፩. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና ኮሌጆችን በሚመለከት የአስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ ከነበረው የማስተባበርና የመምራት ኃላፊነት ጋር ተያይዞ የተፈጠሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኤጀንሲው ተላልፈዋል፣

፪. የአስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ በተመለከተው መሰረት ለኤጀንሲው የተላለፉትን መብትና ግዴታዎች አስመልክቶ ያሉትን መዛግብት ሰነዶችና ሌሎች መረጃዎች ለኤጀንሲው ያስረክባል።

**፳፮. ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ የከተማው አስተዳደር ካቢኔ ሊያወጣ ይችላል።

**፳፯. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች**

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም የአስተዳደሩ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

**፳፰. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከመስከረም ፪ ቀን ፪ሺህ፪ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ

መስከረም ፪ ቀን ፪ሺህ፪ ዓ.ም

ኩማ ደመቅሳ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

**25. Transfer of rights and obligations**

1. The rights and obligations of the Education Bureau of the City Government concerning technical and vocational education and training institutions and colleges are transferred by this Proclamation to the Agency;
2. The Education Bureau of the City Government shall, in accordance with Sub-Article 1 of this Article, handover to the Agency all documents and records and other information related to the rights and obligations transferred to the Agency,

**26. Power to Issue Regulation**

The city Cabinet may issue regulation for the implementation of this Proclamation.

**27. Inapplicable Laws**

Any proclamation, regulation, directive or customary practice of the City Government contradicting this Proclamation shall not be applicable on issues covered by this Proclamation.

**28. Effective Date**

This Proclamation shall come in to force as of the 12th day of September, 2009.

**Done at Addis Ababa**

**This 12th day of September 2009**

**Kuma Demeksa**

**Mayor of Addis Ababa City**